
ጽሑፍ እና ሥዕል፡- ዊልያም ዴ ቪንክ

# መሲሑ ኢየሱስ




ዓለምን የለወጠው አምላክ ሰው

# ዋና ዋና ቃላት. .




ኃጢአት - እኛ የምንፈጽመው ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የማይስማማና እርሱ ወዳኖረልን ግብ እንዳንደርስ የሚያግደን ነገር (ገጽ 4)

መልአክ - የማይታይ የእግዚአብሔር መልእክተኛ (ገጽ 5)




መመለስ - ኢየሱስ ወደ ምድር ሲመለስ ማንኛውም ነገር አዲስ ይሆናል። እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ያድሳል (ገጽ 57)።



መሲሕ - ‹‹የተቀባ ንጉሥ›› መሲሕ የዕብራይስጥ ቃል ሲሆን፣ በግሪክ ክርስቶስ ተብሎ ተተርጉሞአል። (ገጽ 52፣ 55)።

መስቀል- በገዛ ራሱ ፈቃድ ኢየሱስ የሞተበት የማሰቃያ መሣሪያ፤ ከኢየሱስ ሞት ወዲህ መስቀል የተከታዮቹ ሁሉ ምልክት ሆኗል (ገጽ 25, 50)።




መንፈስ ቅዱስ - የኢየሱስ ተከታዮች በሆኑ ሰዎች ውስጥ የሚኖር የእግዚአብሔር መንፈስ (ገጽ 58)።



መጽሐፍ ቅዱስ - እግዚአብሔር ሰዎችን ስለሚያይበትና ከእነርሱም ጋር ስለሚያደርገው ግንኙነት ከመጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ ይቻላል።

ሰይጣን - የማይታይ የእግዚአብሔርና የሰዎች ጠላት፤ ዲያብሎስ ተብሎም ይጠራል።



በረከት - እርሱ የሚፈልገውን ለሚያደርጉ ሰዎች እግዚአብሔር የሚሰጠው መልካም ነገር ሁሉ።

ትንሣኤ - ኢየሱስ ከሞት መነሣቱ፤ አንድ ቀን ደግሞ ሰዎች ሁሉ ከሞት ይነሣሉ፤ ከዚያም እግዚአብሔር በእያንዳንዱ ሰው ይፈርዳል (ገጽ 53-57)።

ኢየሱስ - የእግዚአብሔር ልጅ ስም ሲሆን፣ ‹‹እግዚአብሔር ያድናል›› ማለት ነው።

እምነት - እግዚአብሔር የተናገረው ቃል እንደሚፈጸም አምኖ መቀበል።

የእግዚአብሔር ልጅ - ይህ የኢየሱስ ስም ነው። እርሱ ሰው በመሆን ወደዚህ ምድር የመጣ የእግዚአብሔር ልጅ ነው።

የእግዚአብሔር መንግሥት - ሰዎች ለእርሱ በሚታዘዙበት ቦታ በዚያ የእግዚአብሔር መንግሥት ይኖራል።

የዘላለም ሕይወት እግዚአብሔር ባቀደው መሠረት ከኢየሱስ ጋር የምንኖረው ሕይወት። ሞትን ያሸንፋል፤ ማለቂያም የለውም (ገጽ 23፣ 29-30 እና 59)


የጌታ ራት - በእንጀራውና በወይኑ አማካይነት የኢየሱስ ተከታዮች የእርሱን ሞትና ትንሣኤ የሚያስታውሱበት

ይቅርታ - ምንም እንኳ የሚገባን ባይሆንም፣ እግዚአብሔር ይቅር ይለናል፤ በኃጢአታችን ከተጸጸትንና ከዚያ ለመመለስ ፈቃደኛ ከሆንን እግዚአብሔር ይቅር ይለናል። ኢየሱስ እኛ የሚገባንን ቅጣት ስለ ተቀበለ ይቅር መባል እንችላለን (ገጽ 58)።

ደቀ መዝሙር - የኢየሱስ ተከታይ (ገጽ 18)

ጸሎት - ጸጥ ብለን ወይም ድምፃችንን በማሰማት ለእግዚአብሔር መናገርና ከእርሱም መስማት (ገጽ 18፣ 19፣ 42)።

ፋሲካ - የኢየሱስ ትንሣኤ የሚከበርበት በዓል። አይሁድም ፋሲካን የሚያከብሩት በዚሁ ቀን ነበር።



## መሲሕ ኢየሱስ ማን ነው?


ከ2,000 ዓመት በፊት ኢየሱስ በእስራኤል ይኖር ነበር። ‹መሲሕ ኢየሱስ› ወይም፣ ‹ኢየሱስ ክርስቶስ› በማለት እንጠራዋለን። እርሱ ንጉሥ ቢሆንም፣ ንጉሥ ብቻ አልነበረም። ኢየሱስ፣ ‘የእግዚአብሔር ልጅ’ ተብሎም ይጠራል፤ ከዚያም በላይ እርሱ፣ ‹‹የሰው ልጅም›› ነው። ይህም ማለት እርሱ እግዚአብሔርም ሰውም ነው ማለት ነው። የኢየሱስ ሕይወት ታሪክ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፏል። ይህ የዘመናት ሁሉ ትልቁ ታሪክ ነው።

## ኢየሱስ የመጣበት ዘመን

ዘመናችን የሚጀምረው ከኢየሱስ መወለድ ነው። በዚያ ዘመን ሰዎች የሚጓጓዙት በእግር ወይም በአህያ፣ በግመል ወይም በፈረስ ነበር። አብዛኛው የአውሮፓ፣ የመካከለኛው ምሥራቅና የሰሜን አፍሪካ ክፍል በሮም መንግሥት ተይዞ ነበር። አብዛኛው ሕዝብ ማንበብ መጻፍ አይችልም ነበር፤ ማንበብ መጻፍ የሚችሉት በእስራኤል ምድር የነበሩ አይሁድ ነበሩ። እነዚህ ሰዎች፣ ‘የመጽሐፉ ሰዎች’ ይባሉ ነበር።

እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስ በሚባለው መጽሐፍ በኩል ይናገራል። እርሱ ሕልውና ያላቸው ነገሮች ሁሉ ፈጣሪ ሲሆን፣ የሰዎች ሁሉ ወዳጅ መሆን ይፈልጋል። ኢየሱስ ይህን በግልጽ አሳይቷል!






# እስራኤል በኢየሱስ ዘመን

ዋና ከተማ ኢየሩሳሌም

አውራጃዎች ገሊላ፣ ሰማርያ፣ ይሁዳ

ስፋት በግምት 28,000 ኪሎ ሜትር ወይም 10,810 ስኩዌር ማይሎች


የአየር ሁኔታ ከፊል ሐሩራዊ

የፖለቲካ ሁኔታ፣ ከኢየሱስ መወለድ በፊት ከነበረው ጊዜ ማለት በ63 ዓቅክ (ዓመት ቅድመ ክርስቶስ) ጀምሮ እስራኤል በሮማውያን ቁጥጥር ሥር ነበረች።


በዘመኑ የነበሩ ገዦች ሮማዊው ባለ ሥልጣን ጴንጤናዊው ጲላጦስ እስራኤል ይገዛ ነበር፤ የእርሱ አለቃ ሮማዊው ንጉሥ ጤባሪዮስ ነበር።

ሃይማኖት ይሁዲነት። አይሁድ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ነበራቸው። ማንኛውንም ሃይማኖታዊ ሥራ የሚያከናውኑ ካህናት ነበሩ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ሕዝቡን የሚያስተምሩ ፈሪሳውያን የመሳሰሉ አስተማሪዎች ነበሩ።

ቋንቋዎች የአይሁድ ቋንቋ ዕብራይስጥ ሲሆን፣ ግሪክ የዚያ አካባቢ ሕዝብ ሁሉ ቋንቋ ነበር፤ ላቲን የሮማውያን ቋንቋ ነበር።



እነዚህ ሰዎች ሁሉ ወንዙ ዳር የተሰበሰቡት ለምንድነው?
የእግዚአብሔር መንግሥት መጥታለች፤ ራሳችሁን አዘጋጁ!


አዲስ ሕይወት ይኑራችሁ!
የእግዚአብሔር ፍርድ መጥረቢያ ዛፎች ሥር ተቀምጧል...
መልካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ሁሉ ተቆርጦ ወደ እሳት ይጣላል!
እኛ ሁላችንም ልንቆረጥ እንችላለን፤ ታዲያ፣ መልካም ሕይወት መኖር የሚችል ማን ነው?
ትክክል! ማንም ከእግዚአብሔር ፍርድ ማምለጥ አይችልም። ነገር ግን ከእኔ በኋላ ሁለንተናችሁን መለወጥ የሚችል ይመጣል።
በእውነት ሕይወታችሁ እንዲለወጥ ከፈለጋችሁ፤ ኃጢአተኞች መሆናችሁን ተቀበሉ፤ ከዚያ ወደዚህ ውሃ መጥታችሁ ተጠመቁ!
አሁን ከኃጢአታችሁ ነጽታችኋል፤ ስለዚህ አዲስ ሕይወት መኖር ጀምሩ!


ወንዙ ዳር የነበረውን ሰባኪ ሰዎች መጥምቁ ዮሐንስ ይሉት ነበር...
እኔ ይህን ያህል አስፈላጊ ወይም ጠቃሚ አይደለሁም፤ እኔ የእግዚአብሔርን ማንነት ለሚያሳየን ለእርሱ መንገድ እያዘጋጀሁ ነው። እርሱ በእግዚአብሔር መንፈስና በእግዚአብሔር እሳት ያጠምቃችኃል። ያኔ ሁለንተናችሁ ይለወጣል!
ከዚያም...
... ይልቁን እኔ በአንተ መጠመቅ አለብኝ!
ግዴለም አንተ አጥምቀኝ፤ እንዲህ በማድረግ እግዚአብሔር የሚፈልገውን እንፈጽማለን።
አባት ሆይ፣ መንግሥትህ ትምጣ፤ የአንተ ፈቃድ ይፈጸም!
ከሰማይ እንዲህ የሚል ድምፅ መጣ...
አዎን፣ አንተ ልጄ ነህ፤ እወድሃለሁ፤ በአንተም ደስ ይለኛል።


መጥምቁ ዮሐንስ ለሚመጣው መሲሕ እስራኤልን እያዘጋጀ የነበረው የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት ነበር፤ በዚያ ዘመን እስራኤል በጣም ሰፊ በነበረው በሮም መንግሥት ውስጥ በጣም ትንሽ ቦታ የያዘች ነበረች።
እስራኤል
ቅፍርናሆም
ናዝሬት
ቃና
ገሊላ
ዮርዳኖስ
ኢየሩሳሌም
ይሁዳ
በእስራኤል የነበሩ አይሁድ ጭቆና ውስጥ ነበሩ፤ ከዚያ ለመላቀቅ ዐቅም አልነበራቸውም። ሕዝቡ መሲሑ የሚመጣበትን ጊዜ እየተጠባበቁ ነበር፤ እርሱ እንደሚመጣ በጥንታውያን የአይሁድ መጻሕፍት ትንቢት የተነገረለት አዳኝ ነው። ይህ መሲሕ የእግዚአብሔር ፍትሕ አሸንፎ እንዲወጣ ያደርጋል።
በዮርዳኖስ ወንዝ የነበረው መጥምቁ ዮሐንስ ወደ ኢየሱስ በማመልከት...
ተመልከቱ! የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚብሔር በግ ይኸውና አለ።
ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ የእግዚአብሔር መንፈስ ወደ ምድረ በዳ መራው።
እርሱም በዚያ ዐርባ ቀንና ዐርባ ሌሊት ቆየ፤ በዚያ ቆይታው ምንም አልበላም። የሚጠብቀው ሥራ ምን እንደ ነበር በግልጽ ለማየት ሲጸልይና ሲጾም ነበር።
ኢየሱስ ዓለምን በሞትና በጥፋት ይገዛ የነበረው የማይታየው ጨለማ ገዢ ሰይጣንን ተቃወመ።
በዚያ ሁኔታ ሲያልፍ ኢየሱስ በዓለም ውስጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ግልጽ ማድረግ ነበረበት። የእግዚአብሔር ዕቅድ ሰዎች ከሞት ማነቆ ነጻ እንዲወጡ ነው።
አዎን፣ አባት ሆይ፣ አንተ የምትፈልገ ውን አደርጋለሁ!


ነገር ግን ተቃዋሚው ሰይጣን የእግዚአብሔርን ተልዕኮ ከመፈጸም ሊያዘናጋው ወደ ኢየሱስ አሳሳች ሐሳቦች ማምጣት ሞከረ።
በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ እስቲ እነዚህን ድንጋዮች ዳቦ አድርጋቸው!
በፍጹም አላደርገውም! ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል እንጂ ሰው በእንጀራ ብቻ እንደማይኖር መጽሐፉ ውስጥ ተጽፎአል።
አንተ በእርግጥ የእግዚአብሔር ልጅ መሆንህን በተግባር አሳይ! ከቤተ መቅደሱ ጣራ ወደ መሬት ዝለል። የእግዚአብሔር መላእክት እንደሚያነሡህ ተጽፎአል አይደል?
እግዚአብሔርን አትፈታተን ተብሎም ተጽፏል።
አንተ ወድቀህ ብትሰግድልኝ፤ በምድር ያለውን ሥልጣንና ኃይል ሁሉ እሰጥሃለሁ!
አንተ ሰይጣን ከእኔ ራቅ! እኛ ማምለክና ማገልገል ያለብን እግዚአብሔርን ብቻ እንደ ሆነ ተጽፎአል።
ከዚያም ሰይጣን ከኢየሱስ ተለይቶ ሄደ፤ መላእክትም መጥተው አገለገሉት...
ኢየሱስ ወደ ገሊላ የተመለሰው በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ነበር። ኢየሱስ ያደገው ብዙ ሕዝብ ይኖር በነበረበት ሰሜናዊ የእስራኤል አውራጃ ነበር። እየተጓዘ እያለ ብዙዎች አብረውት ሆኑ። ኢየሱስ ነቢያት ትንቢት የጻፉለት መሲሕ መሆን አለመሆኑን ለማየት ጓጉተው ነበር።



በኮረብታማው የገሊላ አካባቢ ባለው ቃና በሚባል ቦታ ሰርግ ነበር...
ኢየሱስና እናቱ ከጥቂት ወዳጆቹ ጋር ወደ ሰርጉ ተጠርተው ነበር።


ግን ግብዣው እየተደረገ መሐል ላይ...
ችግር ተፈጠረ! ወይን ጠጁ አለቀባቸው!
ኢየሱስ የሚነግራችሁን አድርጉ!
ትልልቅ እንስሮቹን ውሃ ሙሏቸውና የግብዣው አሳላፊ እንዲቀምስ ሰጡት።
?
ውሃ አልነበረም እንዴ? አሁን ግን ወይን ጠጅ ሆኗል! ለዚያውም ምርጥ ወይን ጠጅ!
ቅመሰው! ምርጡን ወይን ጠጅ እስከ አሁን ድረስ አቆይተሃል!
እንዲህ ያለ ነገር ሰምቼ አላውቅም! ይህን በሚመስል ሰርግ ተገኝቼ አላውቅም፤ ወደ ምርጥ ወይን ጠጅ የተለወጠ ውሃ ጠጥቼ አላውቅም!
ይህ የናዝሬቱ ኢየሱስ ሥራ ነው?
ለመሆኑ፣ እርሱ ማን ነው?


ቅፍርናሆም ገሊላ ባሕር አጠገብ የምትገኝ ሀብታም የዓሣ ማጥመጃ ሰፈር ናት። ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት በተመለከተ በአደባባይ መናገር የጀመረው እዚህ ነበር!
የመጀመሪያዎቹን ደቀ መዛሙርት የመረጠው እዚህ ነበር።
ጴጥሮስ፣ ወደ ጥልቁ ባሕር እንቅዘፍና መረብህን ጣል።
ጌታ ሆይ፣ ሌሊቱን ሁሉ ስንደክም ብናድርም ምንም አልያዝንም።
አንተ ከተናገርህ ግን...
በፍጹም ማመን አልችልም።


ያዕቆብ! ዮሐንስ! ወደዚህ ኑ፤ ለዕድሜ ልካችን የሚበቃ ዓሣ አጥምደናል!
ጌታ ሆይ፣ በጣም ኃጢአተኛ ስለሆንሁ ከእኔ ተለይ።
ጴጥሮስ፣ አትፍራ!
ይልቅ መጥተህ ተከተለኝ፤ ሰዎችን የምታጠምድ አደርግሃለሁ!
ተከተለኝ!


ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ለሰው ሁሉ እየተናገረ፣ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በመላው ገሊላ ተመላለሰ። ማንኛውንም ዐይነት ደዌ ፈወሰ፤ አጋንንታዊ መንፈሶችን አስወጣ፤ ሰዎቹም በጣም ተደንቀው ተከተሉት፤ ከሌሎች አካባቢዎችና የእስራኤል ዋና ከተማ ከሆነችው ከኢየሩሳሌም እንኳ ሳይቀር ሰዎች እየመጡ ነበር። እርሱ የሚናገረውንም ሁሉ ሰሙ…
መንግሥተ ሰማይ የእነርሱ ስለ ሆነች ድኾች የተባረኩ ናቸው።
ጽድቅን የሚራቡ የተባረኩ ናቸው፤ ይጠግባሉና።
የሚያለቅሱ የተባረኩ ናቸው፤ እንደ ገና ይስቃሉና።
በእኔ ምክንያት ሰዎች ሲነቅፏችሁ የተባረካችሁ ናችሁ፤ ዋጋችሁ በሰማይ ታላቅ ስለሆነ ደስ ይበላችሁ ሐሤትም አድርጉ።



ለእናንተ እንዲደረግላችሁ እንደምትፈልጉት እናንተም ለሰው ሁሉ አድርጉ።
ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ ደግሞም ጸልዩላቸው።
መልካም ነገር ስታደርጉ የሰዎችን ትኩረት ለመሳብ ብላችሁ አታድርጉ፤ በስውር አድርጉ።
ከእርሷ ጋር ለመተኛት በመጓጓት ወደ ሴት የሚመለከት፤ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሮአል።
ዐይን የሰውነት መብራት ነው፤ ዐይንህ ጤነኛ ከሆነ መላው አካልህ ብሩኅ ይሆናል። ዐይንህ በጭጋግ ከተጋረደ ግን በጨለማ ትኖራለህ።
ማንም ለሁለት ጌቶች መገዛት አይችልም፤ እግዚአብሔርንና ገንዘብን ማገልገል አይቻልም።
ስለ ነገ አትጨነቁ።፡ በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን መንግሥት አስቀድሙ፤ ሌላው ነገር ሁሉ ተከትሎ ይመጣል።
ቃሎቼን ብትከተሉ ቤቱን በዐለት ላይ እንደ ሠራ ሰው ትሆናላችሁ፤ ቃሎቼን የማትከተሉ ከሆነ ግን ቤቱን አሸዋ ላይ እንደ ሠራ ሰው ትሆናላችሁ።



አንድ ቀን ሰዎች ቅፍርናሆም ኢየሱስ ወደ ነበረበት ቤት መጥተው ነበር...
በፍጹም መግባባት አንችልም።
አዎን ጣራው ላይ ነው፤ ምንጣፍና ሌላ ነገርም ይታያል!
እዚያ ላይ ምን እየሆነ ነው?
ተዋቸው! እነዚህ ሰዎች ትልቅ እምነት አላቸው!
ኃጢአትህ ይቅር ተባለልህ!
እንዴት እንዲህ ይላል፤ የተናገረውን ሰማችሁ?
እግዚአብሔርን እየተሳደበ ነው!
የሰውን ኃጢአት ይቅር ማለት የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው!
ለመሆኑ ለአካል በሽተኛው ምን ማለት ይቀላል፤ ኃጢአትህ ይቅር ተብሎልሃል ማለት ወይስ ተነሣና በእግርህ ቁም ማለት?
መሲሑ ኃጢአትን ይቅር የማለት ሥልጣን አለው፤ እኔ ግን ጨምሬ፣ ምንጣፍህን ይዘህ ተነሣና ተመላለስ! እላለሁ።


በጣም ይገርማል!
አዎን፣ መራመድ ችያለሁ!
ሰውየው እየተራመደ ነው!
ግን ኢየሱስ ባደረገው ነገር ደስ ያላቸው ሁሉም አልነበሩም። የሃይማኖት መሪዎቹ ኢየሱስ የሰንበትን ደንቦች ያከብር እንደ ሆነ እየጠበቁ ነበር። በእስራኤል በዚህ ቀን ማንኛውንም ዐይነት ሥራ መሥራት በጥብቅ የተከለከለ ነበር።
ይኽ ሰው እጁ የሰለለ ነው፤ ታዲያ፣ በዚህ ቀን መፈወስ ተፈቅዷልን?
እጅህን ዘርጋው!
ተመስገን፣ ተፈውሻለሁ!
ይኽን ሰውዬ ማጥፋት አለብን!
ይኽ ሰው ሕዝቡን እያሳተ እንደ ሆነ ኢየሩሳሌም ላሉት መሪዎች መነገር አለበት።



ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በገሊላ ባሕር በጀልባ እየሄደ ነበር።
ጌታ ሆይ፣ ድረስልን! እየሰጠምን ነው!
ለምን ፈራችሁ? እምነታችሁ የታል?



ጸጥ፣ ረጭ በል!
ጀልባቸውን ባሕሩ ዳር አሰሩ፤ ተራራው ላይ ግን...
የጩኸት ድምፅ




ተራራው ላይ አንድ አጋንንት ያደሩበት ሰው ነበር።
እርሱ እየመጣ ነው!
አዎን፣ እየመጣ ነው!
አዎን፣ አዎን፣ ኢየሱስ ራሱ ነው!
የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ሆይ፣ ከአንተ ጋር ምን ጉዳይ አለኝ?
እናንተ አጋንንታዊ መንፈሶች ልቀቁት!
ስምህ ማን ነው?
ብዙ ስለሆንን ስሜ ሌጌዎን ይባላል
ወደ እነዚያ ዐሣሞች እንድንገባ ፍቀድልን።
ሂዱ!


?
ሙሉ በሙሉ ድኛለሁ!
ሂድ! እኛን ተወን!
ከአንተ ጋር ልምጣ?
አይሆንም እዚሁ ሁን። እግዚአብሔር ያደረገልህን ለሰው ሁሉ ተናገር!



ወልድ በራሱ ምንም ማድረግ እንደማይችል እነግራችኋለሁ። እርሱ የሚያደርገው አብ ሲያደርግ ያየውን ብቻ ነው። የአባቴን ፈቃድ እንጂ፣ የራሴን ፈቃድ አላደርግም። እኔን የላከኝም እርሱ ነው።
ኢየሱስ ለጸሎት ሁሌም ወደ ጸጥተኛ ቦታ ይሄድ ነበር።
ሌሊቱን በጸሎት ካሳለፈ በኋላ ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት መረጠ። ሁለት ሁለት እያደረገ ላካቸው። በአጋንንታዊ ኃይሎችና በደዌ ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጣቸው።
እነዚህ ወንድማማቾቹ ጴጥሮስና እንድርያስ ናቸው...
ወንድማማቾቹ ያዕቆብና ዮሐንስ ...
ፊልጶስና ናትናኤል...



ቶማስና ቀደም ሲል ለሮማውያን ግብር ይሰበስብ የነበረው ማቴዎስ።
ታዴዎስና ሌላው ያዕቆብ...
ተቃዋሚ ጦረኛው ስምዖንና የአስቆሮቱ ይሁዳ።
ሂዱ፤ እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል።
12 ሐዋርያት በጣም ተገርመው ከተላኩበት ቦታ ተመለሱ። ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር ወደ አንድ ገለልተኛ ቦታ መሄድ ፈለገ፤ ሕዝቡ ግን ከእርሱ ተለይተው መሄድ አልፈለጉም።
መከሩ ሰፊ ነው፤ ሠራተኞቹ ግን ጥቂት ናቸው። መከሩን የሚሰበስቡ ሠራተኞች እንዲልክ ወደ መከሩ ጌታ ጸልዩ።


ኢየሱስ እንደ ገና እየተናገረና እየፈወሰ ነበር፤ ቀኑ እየመሸ ነበር...
ፊልጶስ፣ እነዚህ ሰዎች በሙሉ እንዴት ምግብ ማግኘት ይችላሉ? ለምን የሚበሉትን አትሰጣቸውም?
የስምንት ወር ደመወዝ እንኳ እነዚህን ሁሉ ማጥገብ አይችልም!
እዚህ አምስት እንጀራና ሁለት ዓሦች ያሉት ልጅ አለ፤ ያለን ይኸው ብቻ ነው።
ሕዝቡን ሃምሳ ሃምሳ እያደረጋችሁ አስቀምጧቸው።
ኢየሱስ እግዚአብሔርን አመሰገነ...
እንጀራውንና ዓሣውን ቆራረሰ።


ኢየሱስ ያበረከተውን ምግብ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች በሉ...
ይኸ ሰውየ ይመጣል የሚባለው መሲሕ መሆን አለበት።
ንጉሣችን ልናደርገው ይገባል!
ተመልከቱ! ትርፍራፊው 12 መሶብ ሙሉ ሆኗል!
ሕዝቡ ወደየቤታቸው መሄድ አለባቸው፤ እናንተም በጀልባ ሆናችሁ ወደ ማዶ ሂዱ። እኔ ግን እዚሁ ተራራው ላይ ቆይቼ አጸልያለሁ።



በኋላም...
አትፍሩ እኔ ነኝ!
እእእ! መንፈስ መሆን አለበት!
ጌታ ሆይ፣ አንተ ከሆንህስ በውሃው ላይ እየተራመድሁ ወደ አንተ እንድመጣ እዘዘኝ!
ጴጥሮስ ና
ጌታ ሆይ አድነኝ!
ጴጥሮስ ለምን ተጠራጠርህ?


ኢየሱስን ንጉሥ ማድረግ የፈለጉ ሰዎች ነበሩ። በእርሱ መሪነት አገራቸውን የያዙ ሮማውያን ለቅቀው እንደሚሄዱ ተስፋ አድርገዋል። የኢየሱስ ተቃዋሚዎችም እየበዙ ነበር። ዘወትር እርሱን ይነቅፉ ነበር። ሕዝቡን በእርሱ ላይ ማነሣሣትና እርሱን ጨርሶ ማጥፋት ፈልገዋል።
መምህር ወደዚህ መቼ መጣህ?
እኔን የፈለጋችሁኝ ስለ ሰጠኋችሁ ምግብ ነውን?
ለዘለቄታ ለሚኖርና የዘላለም ሕይወትን ለሚሰጥ ምግብ እንጂ፣ በስብሶ ለሚጣል ምግብ አትጨነቁ፡
እኔ የዘላለም ሕይወት የሚሰጥ እንጀራ ነኝ። ዓለም ሕይወት እንዲኖረው የሚሰጠው የእኔ ሥጋ ነው።
ይኸ ሰው እንድንበላ የራሱን ሥጋ የሚሰጠን እንዴት ነው?
የማይረባ!
ኑ ከዚህ እንሂድ!
ሰውን ሁሉ እያሳሳተ ነው።
እናንተም መሄድ ትፈልጋላችሁ?
ጌታ ሆይ፣ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ'ኮ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ!


ኢየሱስ ላይ ተቃውሞ እየበዛ ነው። ኢየሱስ ወንዶችና ሴቶች ከነበሩበት የተከታዮቹ ቡድን ጋር የገሊላ አካባቢን ትቶ ወደ ሌሎች የእስራኤል አካባቢዎች ሄዶ መሥራት ጀመረ።
ገሊላ
ኢየሩሳሌም
እስራኤል
በኋላም ወደ ኢየሩሳሌም አቀና።
እየሄደ እያለ...
ሰዎች ስለ እኔ ምን ይላሉ?
አንተ ነቢይ ነህ ይላሉ።
እናንተስ?
እኔ ማን እንደ ሆንሁ ታስባላችሁ?
አንተ አዳኙ ነህ፤ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ።
ይህን ለማንም አትናገሩ፤ በዚያ መከራ ለመቀበልና ለመሞት መሲሕ ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ ይኖርበታል። በሦስተኛው ቀን ግን ከሞት ይነሣል።


ብዙ ጊዜ ሰዎች የሚገደሉት ከኢየሩሳሌም ከተማ ውጪ ነበር፤ የሚገደሉት በአሰቃቂ ሁኔታ ተሰቅለው ሲሆን፣ ይህ ሮማውያን ወንጀለኞችን የሚቀጡበት መንገድ ነበር።
የእኔ መሆን የሚፈልግ ሁሉ ራሱን ከሌሎች መለየት አለበት፤ መስቀሉን ተሸክሞ እኔን መከተል አለበት።
ሕይወቱን አጥብቆ የሚይዝ ያጣዋል፤ ለእኔ ሲል ሕይወቱን የሚያጣ ግን መልሶ ያገኘዋል።
ይህን ማወቅ አለብህ፤ አንድ እግዚአብሔር ብቻ አለ።
በጣም አስፈላጊው ነገር በሁለንተናህ እግዚአብሔርን መውደድ ነው፤ ራስህን እንደምትወድ ሌሎችንም መውደድ አለብህ!


በዚያ ዘመን በእስራኤል ለምጻሞች የሚኖሩበት ሰፈር ነበር። ለምጽ በጣም የሚያስፈራ የቆዳ በሽታ ነው። ይህ በሽታ ያለባቸው ከጤነኞች ጋር እንዲነካኩ አይፈቀድም ነበር።
ለምጻሞች ሰዎች ከእነርሱ ጋር እንዳይነካኩ ለማስጠንቀቅ፣ በሚሄዱበት ቦታ ሁሉ እየጮኹ ለምጻምነታቸውን መናገር ነበረባቸው።
ለምጻም! ለምጻም!
ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ እባክህ ራራልን!


ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ!
ምርመራ እንዲደረግልህ ወደ ካህን ሂድ
ፈውስ የምናገኘው ያኔ ነውን?
?
!
ተመልከቱ! ተፈውሻለሁ!
ተፈውሰናል!
አዎን!
ሃሌ ሉያ! እግዚአብሔር መልካም ነው! ተመስገን!
የተፈወሳችሁት 10 አልነበራችሁም? ታዲያ ሌሎቹ የታሉ? እግዚአብሔርን ለማመስገን አልመጡም ማለት ነው?
አንተ በሰላም ሂድ! እምነትህ መፈወስ ብቻ ሳይሆን አድኖሃል።


ኢየሱስ እየተጓዘ እያለ በኢየሩሳሌም የነበሩ የአይሁድ መሪዎች እርሱን እንዲሰልሉት ሰዎች ወደ እርሱ ላኩ። የሚያደርገውን ሁሉ ይቃወሙ ነበር።
ከአመንዝራዎችና ከሮማውያን ጋር የሚሠሩ ግብር ሰብሳቢዎችን ከመሳሰሉ ሰዎች ጋር ይቀራረባል...
መሲሕ የጠፉትን ለመፈለግ ለማዳን መጥቷል።
ኢየሱስ በሰንበት ቀን ስለ ፈወሰ...
ተፈወስ!
ሕፃናትም የተለየ ትኩረት አግኝተዋል...
ሕፃናት ወደ እኔ እንዳይመጡ አትከልክሉ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እነርሱን ለመሳሰሉ ሰዎች ናት።


ኢየሱስ ከኢየሩሳሌም ጥቂት ርቃ ወደ ነበረች ቢታንያ ወደምትባል ከተማ ተጠራ፤ አልዓዛር ታምሞ ነበር። አልዓዛር፣ ማርያምና ማርታ የሚባሉ ሁለት እኅቶች የኢየሱስ ወዳጆች ነበሩ። ኢየሱስ ቢታንያ ሲደርስ አልዓዛር ከአራት ቀን በፊት መሞቱን ሰማ።
ጌታ ሆይ፣
ጌታ ሆይ፣ አንተ እዚህ ኖረህ ቢሆን ኖሮ ወንድሜ አይሞትም ነበር!
ማርታ ወንድምሽ ከሞት ይነሣል።
አዎን፣ በመጨረሻው ቀን ትንሣኤ ከሞት እንደሚነሣ ዐውቃለሁ።
ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚያምን በሕይወት ይኖራል። ማርታ ይህን ታምኛለሽ?
አዎን ጌታ ሆይ! አንተ ወደ ዓለም እንደሚመጣ የተነገረለት አዳኙ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ።
የት ነው የቀበራችሁት?
ጌታ ሆይ፣ መጥተህ እይ!



ምን ያህል ይወደው እንደ ነበር ተመልከቱ።
አልዓዛር እንዳይሞት ማድረግ ይችል አልነበረምን?
የሞተው ሰው በጨርቅ ተጠቅልሎ ከዐለት በተሠራ መቃብር ውስጥ ተቀምጦ ነበር።
ድንጋዩን አንሡት!
ጌታ ሆይ፤ ከተቀበረ አራት ቀን ስለሆነው ይሸታል...
የእግዚአብሔርን ክብር ታያለሽ
አባት ሆይ፤ ይህን የምለው እዚህ የቆሙት አንተ እንደ ላክኸኝ እንዲያምኑ ነው።
አልዓዛር ሆይ፤ ና ውጣ!
የተጠቀለለበትን ጨርቅ ፍቱለትና ይሂድ።




የኢየሱስና የተከታዮቹ ጉዳይ ኢየሩሳሌም ያሉትን ባለሥልጣኖች በጣም እያሳሰባቸው ነው።
ሰውየው ብዙ ተአምራት እያደረገ ነው።
ይህ ሁሉ ሲሆን ዝም ብለን ካየን፣ ሮማውያን ርምጃ መውሰዳቸው አይቀርም!
ቤተ መቅደሳችንና ሕዝባችንን ያጠፋሉ!
የማመዛዘን ችሎታችሁን ተጠቀሙ! አገሩ ሁሉ ከሚጠፋ አንድ ሰው ለሕዝቡ ቢጠፋ ይሻላል።
ኢየሱስ መሞት ያለበት በዚህ ምክንያት ነው!
ከዚያን ጊዜ ወዲህ የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስን ለሮማውያን አሳልፈው የሚሰጡበትን ምቹ ጊዜ ይጠብቁ ጀመር። የሞት ቅጣት የመፍረድ ሥልጣን ያላቸው እነርሱ ብቻ ናቸው።


ኢየሱስ በቢታንያ እያለ...
ማርያም!
ያ ሽቶ ከፍ ያለ ዋጋ የሚያወጣ ነው!
ገንዘቡን ለድኾች መስጠት ይሻለን ነበር!
ይሁዳ፣ እርሷን ተዋት፤ ሥጋዬን ለመቃብር እያዘጋጀችው ነው።



በቅርቡ የፋሲካ በዓል ይከበራል፤ በጣም ብዙ ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም መምጣታቸው አይቀርም።


በኢየሩሳሌም መሪዎቹ ኢየሱስን ለመያዝ እያሴሩ ነበር፤ ያም ሆኖ እርሱ ወደ ከተማ ለመሄድ ጉዞ ጀምሯል።



ሕዝቡም በደስታና በሆታ ተቀበለውታል።
እንኳን ደኅና መጣህ!
እንኳን ደኅና መጣህ!
በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው!
አንተ የእስራኤል ንጉሥ!
ኢየሩሳሌም! ሰላምን እንዴት እንደምታገኚ ብታውቂ ኖሮ! ነገር ግን አትፈልጊም!
በዚህ ሁኔታ የትም መድረስ አንችልም።
ዓለም ሁሉ እየተከተለው ነው’ኮ


በዋናው ከተማ ያለው ቤተ መቅደስ፤ የአምልኮ ማዕከል ነበር።
የፋሲካ በዓል በሚከበርበት ጊዜ፣ ብዙ በጐች ይታረዳሉ።
ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ጋር ለማስታረቅ፣ በጐች ቤተ መቅደሱ ውስጥ መሥዋዕት ይቀርባሉ
ግን፣ ሕዝቡን ከኃጢአት ነጻ የሚያደርገው የትኛው የመሥዋዕት በግ ይሆን?
ቤተ መቅደሱ አደባባይ ላይ ሰዎች የመነገድና ገንዘብ የመመንዘር ሥራ በዝቶባቸው ነበር።
ኢየሱስም እዚያ ነበር ...


የእግዚአብሔር ቤት የጸሎት ቤት ነው፤ እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችሁት!
አደገኛ ሰው ነው፤ ሰዎች እርሱ የሚለውን ሁሉ ይቀበላሉ።
በተቻለ መጠን ቶሎ እርሱን ማጥፋት አለብን!


በዘዴ ብናጠምደው እጃችን ላይ ይወድቃል፤ ያኔ እኛ በቀላሉ እናስገድለዋለን።
ግን ይህ በበዓሉ ቀን መሆን የለበትም፤ በፋሲካ በዓል ምንም ሁከት እንዲፈጠር አንፈልግም።
እርሱን ይገዤ ባመጣላችሁ ስንት ትከፍሉኛላችሁ?
ይኽ ከኢየሱስ ደቀ መዛሙርት አንዱ የሆነው ይሁዳ ነው!
እንግዲያስ ኢየሱስን አምጥቼ እሰጣችኋለሁ!
ኢየሱስን ይዘህ ብታመጣልን፣ የአንድ ባርያ ዋጋ ማለት 30 ጥሬ ብር እንሰጥሃለን።


ምንም እንኳ መሪዎቹ ያንን ማድረግ አዳጋች ቢያደርጉበትም፣ ኢየሱስ ከፋሲካ በዓል በፊት የነበሩትን ቀኖች በቤተ መቅደስ ለሕዝቡ በመናገር እያሳለፈ ነበር።
በዚያ ምሽት ኢየሱስና 12ቱ ሐዋርያት የፋሲካን ምግብ ለመብላት በከተማው ተገናኝተው ነበር።
በዚህ ሌሊት ዛሬውኑ አደርገዋለሁ!


መከራ ከመቀበሌ በፊት ይህን የፋሲካ ምግብ ከእናንተ ጋር ለመብላት እፈልግ ነበር።
ባለሥልጣኖች ሌሎች እንዲያገለግሏቸው ያደርጋሉ፤ እናንተ ዘንድ ግን እንዲህ መሆን የለበትም።
የሁሉም አገልጋይ የሆነው መሪ ይሁናችሁ።
እኔ በመካከላችሁ ያለሁት እንደ አገልጋይ ነው።


ጌታ ሆይ፣ እንደ አገልጋይ እግሬን ልታጥብ ነው? በፍጹም እንደዚያ መሆን የለበትም!
ጴጥሮስ፣ እኔ ካላጠብሁህ የእኔ መሆን አትችልም።
እንግዲያውስ ጌታ ሆይ፣ እግሬን ብቻ ሳይሆን እጄንና ራሴንም እጠበኝ!
ገላውን የታጠበ ሰው መታጠብ ያለበት እግሩን ብቻ ነው።
እናንተ ጌታና መምህር ትሉኛላችሁ፤ ያ ትክክል ነው። እኔ እግራችሁን እንዳጠብሁ እናንተም አንዳችሁ ሌላውን አገልግሉ።
ከእናንተ አንዱ አሳልፎ ይሰጠኛል።
በፍጹም ሊሆን አይችልም!
መቼም እኔ አልሆንም፤ ነኝ እንዴ?
ይሁዳ ሆይ፣ የምታደርገውን ቶሎ ብለህ አድርግ!


ይህን ዘወትር ለመታሰቢያዬ አድርጉት...
ይህን እንጀራ ብሉ፤ ይህ ሥጋዬ ነው።
ይህን ጽዋ ጠጡ፤ ይህ ለእናንተ የሚፈስ ደሜ ነው። በዚህ መንገድ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር አዲስ ኪዳን ያደርጋል።
አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፤ እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ።
ይህ ፍቅር በእናንተ ዘንድ ቢኖር፣ ሁሉም የእኔ ደቀ መዛሙርት እንደሆናችሁ ያውቃሉ።
ጌታ ሆይ፣ የትም ቢሆን እከተልሃለሁ፤ ለአንተ ስል ሕይወቴን እንኳ እሰጣለሁ።
ጴጥሮስ፣ ዶሮ ከመጮኹ በፊት አንተ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ።



በኋላም በዚያው ምሽት ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ከከተማ ወጡ፤ ይሁዳ ግን ከእነርሱ ጋር አልነበረም...
ከእናንተ ተለይቼ እሄዳለሁ፤ አብ ግን መንፈስ ቅዱስን ይልክላችኋል፤ እርሱ ይረዳችኋል፤ ሁልጊዜም ከእናንተ ጋር ይሆናል።
እኔ የምሄድበትን ቦታ መንገዱን ታውቃላችሁ።
እኔ መንገድ፣ እውነትና ሕይወት ነኝ። በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ማንም ወደ አብ መምጣት አይችልም።
እዚህ ቆዩ፤ እኔ ለመጸለይ ጥቂት ራቅ ብዬ እሄዳለሁ።
አባት ሆይ፤ የሚቻል ከሆነ ይህን መከራ ከእኔ ውሰደው።
ነገር ግን፣ የእኔ ሳይሆን የአንተ ፈቃድ ይፈጸም!




በእንዲህ ዐይነቱ ጊዜ እንዴት ትተኛላችሁ? ተነሡ! አሳልፎ የሚሰጠኝ መጥቷል!
እኔ የምስመውን ያዙት!
እንደምንድነህ መምህር!
ይሁዳ ሆይ፣ በመሳም መሲሑን አሳልፈህ ትሰጣለህን?
ጌታ ሆይ፣ ልዋጋቸው?
አይደለም!
ኢየሱስ እንዲይዙት ፈቀደ፤ ተከታዮቹም በየአቅጣጫው ሮጡ።


ኢየሱስ የአይሁድ መሪዎች ሁሉ የበላይ ወደ ነበረው ሊቀ ካህናት ተወሰደ። ጴጥሮስና ዮሐንስ በሩቅ እየተከተሉት ነበር።
ጴጥሮስ ወደ ግቢው ገባ።
አንተ ከእነርሱ ጋር አልነበርህም?
በፍጹም፣ ሌላው ቀርቶ ሰውየውን እንኳ አላውቀውም።
አንተም ከእነርሱ አንዱ ነህ አይደል?
በፍጹም አይደለሁም!
እዚያ እንደ ነበርህ እርግጠኛ ነኝ! አንተ የገሊላ ሰው አይደለህም?
ምን እያልሽ እንደ ሆነ አይገባኝም።


ኩኩሉ
ከዚያም
እስቲ ትንቢት ተናገርልን፤ ለመሆኑ የመታህ ማን ነው?
ጧት ላይ ኢየሱስን ወደ አይሁድ መሪዎች ጉባኤ አቀረቡት።
አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህን?
ያን ያልኸው አንተ ነህ።
ስድብ ነው! መሞት ይገባዋል፤ ሮማውያን ይፍረዱበት!


ኢየሱስ ጲላጦስ ወደሚባል ሮማዊ ባለሥልጣን ተወሰደ፤ የአይሁድ መሪዎች ሕዝቡን ቀሰቀሱ፤ ማንኛውንም ዐይነት ክስ መሰንዘር ጀመሩ።
ለሚሰነዘርብህ ክስ ሁሉ ምን ትላለህ? ዝም ማለት ብቻ?
ለመሆኑ፣ ያደረግኸው ምንድነው ?
ለእውነት ለመመስከር መጥቻለሁ።
እውነት ምንድነው?
ምንም በደል አላገኘሁበትም፤ እንደምታውቁት የፋሲካ በዓል ሊመጣ ነው። ታዲያ፣ ማንን ልፍታላችሁ፣ በርባንን ወይስ የአይሁድ ንጉሥን?



በርባንን!
በርባንን!
ይኸ ኢየሱስ የሚባለውንስ ምን ላድርገው?
ስቀለው!
ንጉሥ እንደ ሆነ ያስባል!
እርሱን ከፈታኸው እንግዲያው የቄሳር ወዳጅ አይደለህም።
በእርሱ ፈንታ ነጻ ሆነሃል።
በርባን ተፈታ፤ እርሱ በፖለቲካዊ ግድያ ተፈርዶበት ነበር።
...37፤ 38፤ 39!
እኔ ከደሙ ንጹሕ ነኝ።
ሰላም ለአንተ ይሁን የአይሁድ ንጉሥ!


ሰውየውን እዩት!
ስቀለው!
ስቀለው!
ስቀለው!
ጲላጦስ ፍርዱን አጸደቀ። ተሰቅሎ መሞት እጅግ ዘግናኝ ሞት ነበር። ኢየሱስ ይህ የመሰቃያ መሣሪያ የሆነው የመስቀሉን ግንድ ተሸክሞ በኢየሩሳሌም መንገዶች ሄደ።
የመገደያው ቦታ ከከተማው ውጪ ነበር፤ ጐልጐታ፣ ወይም የራስ ቅል ቦታ ይባል ነበር።
እዚያ ወታደሮቹ ኢየሱስን መስቀል ላይ ቸነከሩት።



በዚሁ ጊዜ ይሁዳ ካደረገው ክፉ ነገር የተነሣ በጣም እየተጸጸተ ነበር።
በጣም ተሳስቻለሁ።
ንጹሕ ሰው አሳልፌ ሰጥቻለሁ።
ያ ከእኛ ጋር ምን ያገናኘናል፤ የራስህ ጉዳይ ነው!
ኢየሱስ በሁለት ወንጀለኞች መካከል ተሰቀለ።
አባት ሆይ፣ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው።


መስቀሉ ላይ ‹ኢየሱስ፣ የአይሁድ ንጉሥ› የሚል ጽሑፍ በሦስት ቋንቋዎች ተጻፈ።
IESVS NAZARENVS REX IVDAEORVM
ኢየሱስ ስቃይ ማስታገሻውን መጠጣት አልፈለገም።
ወታደሮቹ ልብሶቹ ላይ ዕጣ ይጣጣሉ ነበር።
የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፣ እስቲ ከመስቀሉ ውረድ!
አዎን፣ ሌሎችን አድኖ አልነበር?
ራስህንና እኛንም አድን!
እግዚአብሔርን ፍራ፣ እኛ የሚገባንን አግኝተናል፣ ይኸ ሰው ግን ምንም በደል አላደረገም።
ወደ መንግሥትህ ስትገባ አስበኝ!
በዛሬው ቀን ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ።


6 ሰዓት ሲሆን ፀሐይ ጨለመች፤ ሁሉም ጨለመ።
የኢየሱስ እናት ማርያምና ደቀ መዝሙሩ ዮሐንስ መስቀሉ አጠገብ ቆመው ነበር።
ከእንግዲህ እናትና ልጅ ናችሁ።
አምላኬ፣ አምላኬ ለምን ተውኸኝ?
ተጠማሁ!
አባት ሆይ፣ መንፈሴን በእጅህ አደርጋለሁ።
ተፈጸመ!



ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ኢየሱስ ሞተ፤ አንዱ ወታደር የኢየሱስን ጐን በጦር ሲወጋው ውሃና ደም ወጣ።
መጽሐፉ፣ ‹‹እንደ በግ ወደ ሞት ተነዳ›› ይላል።
‹‹ስለ መተላለፋችን ተወጋ፤ ስለ በደላችን ደቀቀ።›› አሁን ግን ሞቷል።
እርሱ ይመጣል የተባለው መሲሕ ይሆን እንዴ?
እስቲ እንድንቀብረው ይፈቀድልን ከሆነ እንጠይቅ።
የአርማትያሱ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ የኢየሱስን አስከሬን ወሰዱ፤ ጣፋጭ ቅመም በተነሰነሰበት ናይለን ጨርቅ ጠቅልለው በትልቅ ድንጋይ በተዘጋ መቃብር ውስጥ አኖሩት።


ከሰንበት በኋላ ጥቂት ሴቶች በድንጋይ ወደ ተገጠመው መቃብር ሄዱ...
ድንጋዩ ተንከባልሎ ነበር!
ሕያው የሆነውን ሙታን መካከል ለምን ትፈልጋላችሁ? እርሱ ተነሥቷል፤ ሄዳችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ተናገሩ!
ይህን ሲሰሙ፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ እየሮጡ ወደ መቃብሩ ሄዱ።
ምንድነው የሆነው?
መቃብሩ ባዶ ነው!


መቃብሩ አጠገብ በነበረው አትክልት ቦታ...
አንቺ ሴት ለምን ታለቅሻለሽ? ማንን እየፈለግሽ ነው?
ጌታው፣ አንተ ወስደኸው ይሆን?
ማርያም!
መምህር!
አትያዢኝ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ፣ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ እንደምሄድ ለወንድሞቼ ንገሪ።



በዚያው ቀን ተስፋ የቆረጡ ሁለት የኢየሱስ ተከታዮች ስለ ኢየሱስ መገደል ከአንድ መንገደኛ ጋር እየተነጋገሩ ነበር...
ነቢያትን አታምኑም ማለት ነው? ወደ ክብሩ እንዲገባ መሲሕ መከራ መቀበል የለበትምን? ይህ ሁሉ'ኮ በመጽሐፍ ተጽፏል!
ምግብ እየበሉ እያለ እንግዳው ሰውዬ በድንገት ተሰወረ...
ያ ሰው ኢየሱስ ራሱ ነበር!
ወዲያውኑ ሌሎች የኢየሱስ ተከታዮችን ለማግኘት ሄዱ።
ጌታን አይተነዋል!
ማርያምና ጴጥሮስም አይተውታል!
በድንገት...
ሰላም ለእናንተ ይሁን!
እኔ መሆኔን አታምኑም? እጆቼንና እግሮቼን ተመልከቱ!
ጌታዬና አምላኬ!


በሚቀጥሉት 40 ቀኖች ውስጥ
ኢየሱስ ለተከታዮቹ ተገለጠ፤
በአንድ ጊዜ ከ500 በላይ የሆኑ
ሰዎች አይተውታል። አንድ ቀን
ከሐዋርያት አንዳንዶቹ በገሊላ ባሕር
ዓሣ እያጠመዱ ነበር።
የሚበላ ነገር አላችሁ?
የለም፤ ምንም አልያዝንም!
መረብህን ወደ ባሕሩ ጣል!
በጣም ይገርማል! ብዙ ዓሦች ያዝኩ!
ጌታ’ኮ ነው!
መምህር!
መጥታችሁ ከእኔ ጋር አትበሉም?


ጴጥሮስ፣ በእርግጥ ትወደኛለህ?
ኢየሱስ ጴጥሮስን ይህንኑ ሦስት ጊዜ ጠየቀው...
አዎን ጌታ ሆይ፣ እንደምወድህ ታውቃለህ?
እንግዲያው በጐችን አሰማራ!
ተከተለኝ!
በሰማይና በምድር ሥልጣን ሁሉ ተሰጥቶኛል፤ ወደ ዓለም ሂዳችሁ ሕዝቦችን ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው። በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው፣ የነገርኋችሁን ሁሉ እንዲያደርጉ አስተምሯቸው።
እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ በእያንዳንዱ ቀን ከእናንተ ጋር መሆኔን አትርሱ።
ይህን ከተናገረ በኋላ ኢየሱስ ምድርን ትቶ ወደ ሰማይ ሄደ። ይሁን እንጂ፣ በሕዝቦች ሁሉ ላይ ለመፍረድ እንደሚመጣም ተናግሮአል።

ተከታዮቹ በጸሎት እየተጠባበቁ በኢየሩሳሌም ነበሩ፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው። ኢየሱስ ውስጥ የነበረው ያው መንፈስ አሁን እነርሱም ውስጥ ይኖራል። በኃይልና በሥልጣን ስለ ኢየሱስ የሚመሰክሩ አዲስ ሰዎች ያደርጋቸዋል።









አሁን በመላው ዓለም ያሉ የኢየሱስ ተከታዮች ለመጸለይና መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ ይሰበሰባሉ፤ የኢየሱስን ሞት እንዲያሳስባቸው እንጀራውን ይቆርሳሉ ወይኑን ይጠጣሉ። ልባቸው ውስጥ ያለውን የእርሱን ፍቅር በዙሪያቸው ላሉት ሰዎች እንዲያካፍሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።


ኢየሱስ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያለውን ዓላማ እውን እንዲሆን አድርጓል።
ኢየሱስ ይወደናል! እርሱን ማመስገንና ማምለክ አለብን!
እግዚአብሔር አንድ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለምን ወዶአል፤ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት ይኖረዋል እንጂ ከእንግዲህ አይጠፋም።
WILLEM DE VINK

## መጽሐፍ ቅዱስ

የኢየሱስ ታሪክ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፏል። ከመጽሐፍ ቅዱስ የበለጠ ብዙ ጊዜ የተነበበና በመነበብ ላይ ያለ አንድም መጽሐፍ የለም። መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ መጽሐፎችን የያዘ መጽሐፍ ነው። እነዚህን መጽሐፎች ለመጻፍ 1500 ዓመታት ወስዷል። መጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ የተጠናቀቀው ከ1900 ዓመታት በፊት ነበር። እግዚአብሔር በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ ያደረገውን ተሳትፎ በተመለከተ አያሌ ታሪኮችን አካትቶአል። የኢየሱስ ታሪክ ከምንም የበለጠ የእግዚአብሔርን ማንነት በግልጽ ያሳያል።

## የኢየሱስ ታሪክ



መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ታሪክ የሚናገሩ 4 መጽሐፎችን ይዞአል። መጽሐፎቹ የሚጠሩት በጸሐፊዎቻቸው ስም ነው፡ ጸሐፊዎቹ ሁሉ ኢየሱስ በዚህ ምድር በነበረበት ዘመን የኖሩ ናቸው።

1. ማቴዎስ - የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ነው። ሥራው ቀረጥ ሰብሳቢ ነበር። ኢየሱስ የእስራኤልን ሕዝብ (አይሁድ) በተመለከተ ያደረገውንና የሆነውን ይገልጣል።

2. ማርቆስ - ኢየሱስ ባገለገለበት ዘመን ገና በዐሥራዎቹ ዕድሜ የነበረ ወጣት ነበር፤ ኢየሱስ ከፈጸማቸው ተአምራት በጣም ጥቂቶቹን በጽሑፍ አኑሮልናል።

3. ሉቃስ - የሕክምና ዶክተር ነበር፤ በግል ኢየሱስን አላገኘውም፤ ሰዎችን በተመለከተ ኢየሱስ ያደረገውንና የሆነውን ሉቃስ ይገልጣል።


4. ዮሐንስ - እርሱም የኢየሱስ ተከታይ ነበር፤ በዋነኛነት ደረጃ የኢየሱስን ማንነት ያሳያል። ኢየሱስ ሰዎችን ከኃጢአት ነጻ ለማድረግ ሰው የሆነ እግዚአብሔር ነው።


## የኢየሱስ መወለድ

ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ እናቱ ማርያም ባል ያላገባች፤ ድንግል ነበረች። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ኢየሱስ እንዲወለድ አደረገ። ይህ ተአምር ኢየሱስ ከመወለዱ ረጅም ዓመታት በፊት በመጻሕፍት ተጽፎ ነበር። ኢየሱስ እንደ አንድ ጀግና ወይም ታዋቂ ሰው አልነበረም የተወለደው። ሌላ ምንም ክፍል ስላልነበር እርሱ በረት ውስጥ ነበር የተወለደው።


## የኢየሱስ ተአምራት

ኢየሱስ ብዙ ተአምራት አድርጓል። መጽሐፍ ቅዱስ ከ40 የበለጡ የፈውስ ታሪኮች ይዞአል። በእነዚህ ተአምራት በኩል ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ኃይልና ፍቅር፣ እንዲሁም እርሱ ሰዎችን ለመርዳትና ደስተኞች እንዲሆኑ እንደሚፈልግ አሳየ።





## የኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ



ኢየሱስ የሞተው ለምን ነበር? መልሱ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛል።

ሰዎች ሁሉ አንዳንድ መጥፎ ነገሮች ያደርጋሉ። እነዚህን ነገሮች እግዚአብሔር አይፈልጋቸውም፤ እንዲያውም በጣም ያስቆጡታል ወይም ያሳዝኑታል። እንዲህ ያሉ ነገሮች ኃጢአት ይባላሉ። እነዚህ ኃጢአቶች ሰዎች የእግዚአብሔር ወዳጆች እንዳይሆኑ ያደርጋሉ።
ኢየሱስ የመጣው በዚህ ምክንያት ነበር። በገዛ ራሱ ፈቃድ ኢየሱስ የኃጢአታችንን ቅጣት ወሰደ። ያ ቅጣት ሞት ነበር። ኢየሱስ ለእኛ በመሞቱ እንደ ገና የእግዚአብሔር ወዳጆች መሆን እንችላለን። ይሁን እንጂ፣ በኃጢአታችን ማዘንና መጸጸት አለብን።
ኢየሱስ ከሞት ተነሣ። እግዚአብሔር እንደ ገና ወደ ሕይወት አመጣው። ይህን በማድረጉ እግዚአብሔር ከሞት የበለጠ ብርቱ መሆኑን አሳየ።
አሁን ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር እየኖረ ነው። እርሱ ሕያው ስለሆነ ሁልጊዜ ወዳጃችን መሆን ይችላል። እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ መንገድ መኖር እንድንችል ሊረዳን ይፈልጋል።

### ጸሎት

*በኃጢአትህ አዝነህና ተጸጽተህ ከሆንና የእግዚአብሔር ወዳጅ መሆን ከፈለገህ ይህን የመሰለ ጸሎት ጸልይ፣*
*"እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ ትወደኛለህ።*
*አንድ ልጅህ ኢየሱስን ሰጥተሃል።*
*እኔ ለፈጸምኋቸው ኃጢአቶች በሙሉ እርሱ መስቀል ላይ ሞተ።*
*እባክህን ኃጢአቴን ይቅር በለኝ፤ በኃጢአቴ አዝኛለሁ።*
*ኢየሱስ የእኔ ወዳጅ ስለሆነ ተመስገን።*
*ምንጊዜም የአንተ መሆን እፈልጋለሁ።*
*መኖር እንደምትፈልገው መኖር እንድችል እርዳኝ።*
*ሁሌም ከእኔ ጋር ሁን።*
*ጸሎቴን ስለ ሰማህ ተመስገን።*
*አንተ ቃልህን እንደምትፈጽም ዐውቃለሁ!"*

# ኢየሱስና አንተ

የኢየሱስ ታሪክ መልካም ፍጻሜ አለው። ያኔም ሆነ አሁን በዚህ ዘመን ኢየሱስ የብዙ ሰዎች ወዳጅ ነው። ዓለም ተለውጧል፤ በዚህ ዘመን ሰዎች በመኪናና በአውሮፕላን እንጂ በአህዮች ወይም በፈረሶች አይጓጓዙም። ለኢየሱስ ግን ይህ ልዩነት ምንም ማለት አይደለም። በጥንት ዘመን በእስራኤል እንደ ነበረው ሁሉ ዛሬም እርሱ አጠገባችን ነው።
በዓይን ላይታይ ይችላል፤ ይሁን እንጂ፣ እውን ነው። ዛሬ ወዳጅህ መሆን ይፈልጋል። ልትሰማውና ልትወደው ይገባል።

ስለ ኢየሱስና ከእርሱ ጋር መኖር ስለሚቻለው ሕይወት የበለጠ ማወቅ ትፈልጋለህ? እንደዚያ ከሆነ የሚከተሉትን አድርግ

1. በግልህ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ጀምር፤ ለምሳሌ ከሉቃስ ወንጌል መጀመር ትችላለህ።

2. መጸለይ ጀምር
(ከእግዚአብሔር ጋር ስንነጋገር - ልዩ የሆነ ቃላት መጠቀም አያስፈልግም)

3. ስለ ኢየሱስና ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ለሌሎች ሰዎች ተናገር።የበለጠ መማር እንዲችሉ ተከታዮቹ በአንድነት እንዲገናኙና እርስ በርስ እንዲበረታቱ ኢየሱስ ይፈልጋል።

*ጽሑፍ እና ሥዕል፡- ዊልያም ዴ ቪንክ*
*የቅጅ መብት © እ.ኤ.አ.1993 ስቲችቲንግ ዌሬልድታል፣ ሕዩተን፥ ኔዘርላንድ በደች ቋንቋ "Jezus Messias"ተብሎ ታትሟል።*
*የአማርኛ እትም © እ.ኤ.አ.2018*
*የዲጂታል ቅጂ መብት በCreative Commons BY-SA ፈቃድ ተወስኗል።*
*የሁሉም አገራት የመተርጎም፣ የማባዛት እና የመመለስ መብት የተጠበቀ ነው።*
*ኢሜል: jmpbk.app@gmail.com*



*መሲሑ ኢየሱስ ይህ የኢየሱስ መሲሕ እውነተኛ ታሪክ ነው። እርሱ ከ2000 ዓመታት በፊት በእስራኤል ይኖር ነበር። ከእርሱ ጋር የተገናኙ ሁሉ ይደነቁ ነበር። እርሱ ያደረገውን ማንም አላደረገም። እርሱ የተናገረውን ማንም አልተናገረም። ኢየሱስ በነበረበት ስፍራ ሁሉ ተአምራት ይደረጉ ነበር። እርሱን ለሰሙት ሁሉ ደስታንና ሐሤትን አምጥቶላቸዋል። ግን በድንገት ሁሉም አበቃ። ተቀዋሚዎቹ ገደሉት። ያ ግን የመጨረሻው አልሆነም። ምን እንደ ሆነና የኢየሱስ መሲሕ ታሪክ እንዴት እንደ ቀጠለ አንተ ለራስህ አንብብ!*


*ቋንቋ: አማርኛ (ኢትዮጵያ)*
*language: Amharic (Ethiopia)*
*ISBN: 978-90-73150-62-1*